EthioLion

ፍኖተ ዴሞክራሲ የኢትዮጵያ አንድነት ድምፅ

Finote Democracy Voice of Ethiopian Unity

efdpu@aol.com www. Finote.org

**ፕሮግራም፡-** ረቡዕና እሁድ ከምሽቱ ሁለት ሰዓት አስከ ሶስት ሰዓት በ 13 ሜትር ባንድ

**Program**: Wednesday and Sunday 8:00PM- 9:00 PM on 25 meter band.

# <u>ዜና ዘገባ</u>

**ግንቦት 4 ቀን 2004 ዓ.ም**

**የሙስሊሙ ተቃውሞ ተስፋፍቶ ቀጥሎዋል፤**

**ወያኔም እርምጃ እወስዳለሁ እያለ እያስፈራራ ነው፤**

**ወያኔን በመቃወም እራሱን ነዳጅ አርከፍክፎ ያቃጠለው የፌዴራል ፖሊስ ሞተ፤**

EthioLion.Com

**የወያኔ ቡድን የሙስሊሙ ህብረተሰብ ላነሳው ጥያቄ መመለስ ሲያቅተው በሀይል ለመቀልበስ የጀመረውን እርምጃ ቀጥሎበት ዓርብ ዕለት ሚያዚያ 26 ቀን 2004 ዓ.ም በአዲስ አበባ ከተማ ሁከት ፈጥሮ እንደነበር ታወቀ፡፡**

**የሙስሊሙን ህብተረተሰብ ጥያቄ የፈራው የወያኔ ቡድን ዓርብ ዕለት ሚያዚያ 26 ቀን ብጥበጥ ሊነሳ ይችላል ሌላውንም ህዝብ ሊያነሳሱብኝ ይችላል በሚል ፍራቻ ሐሙስ ሚያዚያ 25 ቀን 2004 ዓ.ም ከደርግ መራር መግለጫ ባልተናነሰ ሁኔታ አስደንጋጭ ማስጠነቀቂያ መስጠቱ ታውቆዋል፡፡**

**በሐይማኖት ሰበብ ድብቅ ዓላማ ለማራመድ የሚሞክር አንድ ቡድን አለ..... እናም እርምጃ እንወስድበታለን....ከዚህ ቡድን ጋር ያበረና አብሮ የተገኘ የአልቃይዳ ሴል ነው......በየመስጊዱ ብጥብጥ ለማስነሳት መሞከር ከባድ የሀገር ክዳት ወንጀል ነው.....የሚሉና ሌሎች የማስፈራሪያ ቃሎችን በመጠቀም መግለጫ ሰጥቶዋል፡፡**

ምንም እንኳዋን የወያኔ ቡድን የሙስሊሙን ህብተሰብ ለማስደንገጥ እና ለማስፋራራት መግለጫ ያወጣ ቢሆንም  ህዝቡ በሰለጠነና በጨዋነት በየመስጊዱ ተቃውሞ ሲያሰማ የዋለ ሲሆን በተለይ በአንዋር መስጊድ ሲቪል የለበሱ የደህንነት ሰዎችን አስርጎ በማስገባቱ የተነሳ ብጥብጦች ተከስተው እንደነበር ከስፍራው ከነበሩ የአይን እማኞች የተገኘው ጥቆማ ያስረዳል።

ይህነኑ ብጥብጥ ተከትሎ የሙስሊም ቆብ ያጠለቁ የደህንነት አባሎች ላይ ሙስሊሙ ድብደባ የፈጸመባቸው ሲሆን በአንጻሩ ግቢውን ጥሰው የገቡ ፖሊሶች በምዕመናኑ ላይ በዱላ ድብደባ መፈጸማቸው ታውቆዋል።

ዓርብ ዕለት የሰላት ስነ ስርዓት ተደርጎ እንዳበቃ እጅግ ወያኔን በሚያስደነግጥ መልኩ ሙስሊሙ አንድ በመሆን ከፍተኛ ተቃውሞ ማሰማት የጀመረ ሲሆን ይህንኑ የህዝቡን ቁጣ የፈራው ወያኔ ከጣና ገበያ እስከ ተክለሀይማኖት አደባባይ......ከሀብተጊዮርጊስ ድልድይ እስከ አራተኛ ፖሊስ ጣቢያ.....ከጎጃም በረንዳ እስከ ምዕራብ ሆቴል...... ድረስ በፌዴራል ፖሊስ እና መትረየስ ባጠመዱ ፓትሮሎች በመክበብ ልዩ ጥበቃ ሲያደርግ እንደነበረም ተስተውሎዋል።

በተመሳሳይ በአወሊያ መስጊድ ህዝቡ ወያኔ ያወጣውን መግለጫ በማናናቅ ከዚህ ቀደም የጀመሩትን ተቃውሞ በበለጠ እና በጠነከረ መልኩ ሲያሰማ የነበረ ሲሆን እዛም ዙሪያውን በእግረኛ ና በፓትሮል ልዩ ከበባ አድርጎ እንደነበር ታውቆዋል።

በዕለቱ በሙስሊሙ ዘንድ ታዋቂ የሆኑ ግለሰቦችን ከየመሀሉ እየመረጡ የሙስሊም አማኞችን ለብጥብጥ ሲቀሰቅሱ ታይተዋል በሚል እያፈሰ ሲወስዳቸው እንደነበርም የአይን እማኞቹ አጋልጠዋል።

አርብ ሚያዚያ 26 ቀን 2004 ዓ.ም ሙስሊሙ በወያኔ ላይ ተቃውሞ እና ውግዘት ሲያሰማ የዋለ ሲሆን ይህንኑ ተከትሎ ምሽት ላይ ወያኔ  ሙስሊሙን ለአመጽ ሲቀሰቅሱ የተገኙ ሁለት የአረብ ሀገር ዜጎች በ24 ሰዓት ከሀገር ውስጥ እንዲወጡ ተደርጓል በማለት በዜና ማወጁ ታውቆዋል።

አስቀድሞ ከምሽቱ ሶስት ሰዓት ላይ በወያኔ ላይ ከፍተኛ ተቃውሞ በማሰማት ግንባር ቀደም የነበሩ የታወቁ የሙስሊም ምሁራኖች ከውጭ ሀገር ዜጎቹ ጋር ግንኙነት አላቸው በሚል ሰበብ በደህንነት ሰራተኞች ከመኖሪያ ቤታቸው ታፍነው መወሰዳቸውን የደረሰን ጥቆማ አጋልጦዋል።

ለሙስሊሙ ሀይማኖት የሚከራከሩትና ብሎም የወያኔን ቡድን የሚቃወሙት ምሁራኖች ምሽት ላይ ታፍሰው ተወስደው በአስኮ መስመር በሚገኝ በመሬት ስር በተሰራ የእስር ቤት ውስጥ እየተሰቃዩ ከአደሩ በሁዋላ  በማግስቱ ወደ ማዕከላዊ ምርመራ እንደወሰዱዋቸው ከውስጥ አዋቂ ምንጮች የተገኘው ጥቆማ ያብራራል።

ወያኔ አህአባሽ የተሰኘውን ብርዝ የሙስሊም እምነት ለማስረጽ የሚያደርገው ሙከራ ክፉኛ ተቃውሞ ከገጠመው ወዲህ በግዴታ እንዲቀበሉ ለማድረግ በገንዘብ እና በተለያዩ መንገዶች ቢጠቀምም አልሳካ ስላለው አሁን ደግሞ በኃይል እርምጃ በመውሰድ ላይ መሆኑ ውቆዋል።





EthioLion.Com

በተለያዩ ከተማ እና መስጊዶች ተጀመረውን የሙስሊሙን እምነት ተቃውሞ ለማፈን መግለጫና የኃይል እርምጃ ቢወስድም አሁን በደረሰን ዘገባ መሰረት በመላ ሀገሪቱ ዋና ዋና ቦታዎች ተቃውሞው ተስፋፍቶ እንደቀጠለ ይነገራል፡፡

ውሀቢያ የተሰኘው የምሁራኖች ስብስብ ከመሆኑም በላይ ስልጣን መያዝ አለብኝ ብሎ እየሰራ ያለ ቡድን ነው ሲል መለስ መግለጫ መስጠቱን ተከትሎ ከትናንት በስቲያ ደግሞ የፌዴራል ጉዳዮች ሚኒስትር ዶ/ር ሽፈራው ተክለርያም የተባለው የወያኔ ተለጣፊ ሙስሊሙ መሀል እየገቡ ቅስቀሳ የሚያደርጉትን ለይተን መመንጠር ጀምረናል በማለት በይፋ እየደነፋ ለህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ገልጾዋል፡፡

ሙስሊሙ በወያኔ ባለስልጣናት ድንፋታና መግለጫ ሳይደናገጥ ከዚህ ቀደም ሲያነሳ የነበረውን ሙስሊሙ የሚመራው እራሱ በመረጣቸው የእምነት አባቶች ብቻ ነው.....የአወሊያ ትምህርት ቤት የፖለቲካ መጠቀሚያ አይሆንም.....ከፖለቲካ ነጻ የሆነ መጅሊስ ይመስረት.....ትግላችን ይቀጥላል የሚሉና ሌሎች መፈክሮችን ሲያሰማ እንደነበረ ለማወቅ ተችሏል፡፡

የሙስሊሙ እንቅስቃሴ ያስደነገጣቸውን የወያኔ ባለስልጣናትን እንዲሁም አባላትንና እና ደጋፊዎችን ለማረጋጋት ሲባል የተነሳውን ተቃውሞ ለአንዴና ለመጨረሻ ግዜ እልባት ሰጥቻለሁ ተረጋግታችሁ ስራችሁን ስሩ በሚል የወያኔው ቁነጮ ምስጢራዊ ደብዳቤ በየመስሪያ ቤቱ መበተኑንም ከተለያዩ መስሪያ ቤቶች የደረሰን ጥቆማ አጋልጦዋል፡፡

በሌላ ዜና የምበላው አጣሁ.....ዘረኝነት በሀገሪቱ ነገሰ....ኢትዮጵያ የጥቂቶች ሀገር ሆናለች..... እያለ በአራዳ ጊዮርጊስ በምኒልክ አደባባይ እራሱን ያቃጠለው የፌዴራል ፖሊስ አባል ህይወቱ ማለፉ ተረጋገጠ፡፡

ሚያዚያ 15 ቀን 2004 ዓ.ም ከቀኑ 11 ሰዓት ላይ የምበላው አጣሁ..... መልካም አስተዳደር ጠፋ...... ዘረኝነት ነገሰ ......የሚሉና ሌሎችን መፈክሮች ሲያሰማ ከቆየ በሁዋላ እራሱን ቤንዚን አርከፍክፎ ያቀጠለው የደቡብ ተወላጁ የፌዴራል ፖሊስ አባል የነበረው ዳዊት ላንዳሞ ለሰባት ቀናት ያህል በሆስፒታል ህክምና ሲደረግለት ቢቆይም የደረሰበት ቃጠሎ ከፍተኛ በመሆኑ ህይወቱ ሊያልፍ ችሎዋል፡፡

ስድስት ኪሎ ሰማእታት ሐውልት ፊት ለፊት በሚገኘው የካቲት 12 ሆስፒታል ውስጥ በህክምና ሲረዳ ቢቆይም ጉዳቱ ወደ ውስጥ የዘለቀ በመሆኑ ህይወቱ ያለፈ ሲሆን አስከሬኑን ማዘጋጃ ቤት ወስዶ የት እንዳደረሰው ለማወቅ እንዳልተቻለም ታውቆዋል፡፡

ዳዊት ላንዳሞ የተባለው የደቡብ ተወላጅ የፌዴራል ፖሊስ አባል የነበረ ሲሆን በተደጋጋሚ ግዜ በሚደረጉ ስብሰባዎች ላይ የህወሀት ሹመኞች የሆኑትን መኮንኖች በጥያቄ የሚያጣድፍ እና የሚያስጨንቃቸው በመሆኑ በመበሳጨታቸው ከሶስት ወር በፊት ከስራ እንዲባረር ያደረጉት መሆኑን የጠቆመው የደረሰን ዘገባ ከዚያን ግዜ ጀምሮ የጎዳና ተዳደሪ ሆኖ እንደነበረም ለማወቅ ተችሎዋል፡፡

EthioLion.Com

ዳዊት ላንዳሞ የሞተው እሁድ ሚያዚያ 21 ቀን 2004 ዓ.ም ከጠዋቱ 1 ሰዓት ከ45 ላይ መሆኑን የጠቆሙት የሆስፒታል ምንጮች አስከሬኑ ወደ ዳግማዊ ምኒልክ ሆስፒታል ከተወሰደ በሁዋላ የማዘጋጃ ቤት ሰራተኞች በድብቅ ምሽት ላይ ከሚኒሊክ ሆስፒታል ወስደው የት እንደቀበሩት እንዳልታወቀ ገልጸዋል።

ከዚህ ቀደም በተመሳሳይ ፍትህ እና ዲሞክራሲ በሀገሪቱ ጠፍቶዋል በሚል የሁለተኛ ደረጃ መምህር የሆነው የኔሰው በብስጭት እራሱን ነዳጅ አርከፍክፎ ያቃጠለ ሲሆን አስከሬኑ ለቤተሰብ እንዳይሰጥ ተከልክሎ ለሳምንት ያህል በጤና ጣቢያ ውስጥ በፖሊስ ሲጠበቅ እንደነበር አይዘነጋም።

EthioLion.Com